በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ

ለቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት

መመሪያ ቁጥር 125/2014

የብድር አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 125/2014

ሚያዚያ 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሚያከናውኗቸው ዋና ዋና ተግባራት አንዱ የብድር አገልግሎት በመስጠት የአባላትን የገንዘብ እጥረት ችግር በመፍታት በሙሉ አቅማቸው በመስራትና ዓላማቸውን ለማሳካት የአባሎቻቸውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች በዘላቂነት የሚፈቱበትን አቅም ማጐልበት በማስፈለጉ፤

የህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጡትን የብድር አገልግሎት ፍትሃዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ህብረት ስራ ማህበራት የብድር አገልግሎት ከመስጠታቸው በፊት የብድር አገልግሎቱን በአግባቡ መምራት የሚያስችል የብድር መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ የተሻሻለው የአሰፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ በአዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 2 ፊደል

ተራ ሠ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረት ስራ ኤጀንሲ የቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት የብድር አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 125/2014 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   1. **“አዋጅ”** ማለት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ነው፣
   2. **“የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ”** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ ለቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት የወጣ የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ ማለት ነው፣

3. **“መተዳደሪያ ደንብ”** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ ለቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት የወጣ ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ማለት ነው፣
4. **“ኅብረት ስራ ማህበር”** ማለት ሰዎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ፣ባህላዊ እና ሌሎች የጋራ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላትና በተናጠል ሊፈቱ ያልቻሏቸውን ችግሮች ለማቃለል በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ህጋዊ ሰውነት ያለው የህብረት ስራ ማህበር ነው
5. **“አባል”** ማለት በኅብረት ስራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀጽ 2 እና3 መሰረት የኅብረት ስራ ማህበር አባልነት መመዘኛዎችን አሟልቶ የተመዘገበ ማንኛውም ግለሰብ ወይም በአዋጅ ቁጥር 985/2009 መሰረት ተቋቋመ ኅብረት ስራ ማህበር ነው፣
6. **“ዕጣ”** ማለት በህብረት ስራ ማህበሩ የታወጀ እኩል ዋጋ ያለውና ለአባልነት እንደ

መጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ በጥሬ ገንዘብ የተሸጠ ወይም የሚሸጥ ነው፣

7. **"ቁጠባ"** ማለት የኀብረት ስራ ማህበር አባል ከሚያገኘው ገቢ ውስጥ ቀንሶ በኀብረት ስራ ማህበሩ የሚያጠራቅመው ገንዘብ ነው፣

8. ***"መደበኛ ቁጠባ"*** ማለት የቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማህበሩ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ እና ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ አባሉ በግሉ የወሰነውን የቁጠባ መጠን በተከታታይነት ያለማቋረጥ የሚቆጠበው ቁጠባ ነው ፡፡

9. ***"መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ"*** ማለት አባሉ በፍላጎቱ ከመደበኛው ቁጠባ በተጨማሪ በተለያዩ የቁጠባ አይነት የሚቆጥበው ቁጠባ ነው፡፡

10. **"ተሳትፎ"** ማለት አንድ አባል በህብረት ስራ ማህበሩ ውስጥ በመተዳደሪያ ደንቡ በተቀመጠው መሰረት ከኀብረት ስራ ማህበሩ ጋር የሚያደርገው መስተጋብር ነው፡፡

11. **“ብድር”** ማለት አባላት ለተለያዩ ጉዳዮች ማስፈጸሚያ የሚሆን ከቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም ከፋይናንስ ተቋማት በሚደረግ ስምምነት መሰረት በተወሰነ ጊዜ ቆይታ ተመላሽ የሚሆን እና ወለድ የሚያስከፍል ወይም ወለድ የማያስከፍል ገንዘብ ነው፡፡

12. **“ያልተመለሰ ብድር”** ማለት ብድር ተሰጥቶ እንዲመለስ በውል ከተወሰነበት ጊዜ ከ30 ቀን በላይ ሳይመለስ ያለፈው ብድር ነው፣

13. **“የማይመለስ ብድር”** ማለት ብድር ተሰጥቶ እንዲመለስ በውል ከተወሰነበት ጊዜ ከ12 ወር በላይ ያልተመለሰ ብድር ነው፣

14. **“የማይመለስ ብድር መጠባበቂያ”** ማለት የህብረት ስራ ማህበሩ በመተዳደሪያ ደንቡ በወሰነው መሰረት ከሰጣቸው ብድሮች ውስጥ ያልተመለሰና ለማይመለስ ብድር ማካካሻ የሚሆን ከጠቅላላው ገቢ ተቀንሶ የሚቀመጥና በወጪ የሚያዝ ገንዘብ ነው፣

15. **“ወለድ”** ማለት ግለሰቦች ወይም ተቋማት ለቆጠቡት ገንዘብ የሚከፈላቸው ወይም ለተበደሩት ገንዘብ የሚከፍሉት ዋጋ ነው፡፡

16. **“ወለድ አልባ የብድር አገልግሎት” ማለት** በሸሪያ ህግ መሰረት በሚሰጡ የብድር አገልግሎቶች ወለድ መቀበልና መክፈልን በጥብቅ የሚከለክል አገልግሎት ማለት ነው፡፡

17. **“የብድር ዋስትና”** ማለት ተበዳሪው ከኅብረት ስራ ማህበሩ ብድር ሲወስድ ብድሩን ለመመለስ የማይችልበት ሁኔታ ሲፈጠር የብድር ያለመመለስ አደጋን ለመቀነስ በመያዥነት የሚቀርብ የንብረት ወይም የሰው ዋስትና ነው፣

18. **“የብድር ውል”** ማለት በህብረት ስራ ማህበሩ እና በተበዳሪው መካከል የሚፈፀም ህጋዊ ውልና የስምምነት ሰነድ ነው፣

19. **“የእፎይታ ጊዜ”** ማለት አንድ ተበዳሪ ብድሩን ከወሰደ በኃላ እዳውን መክፈል ከመጀመሩ በፊት የሚሰጥ ጊዜ ነው፡፡

20. **“የአዋጭነት ጥናት”** ማለት ተበዳሪው አካል የሚበደረውን ገንዘብ የሚያውልበትን የስራ ዘርፍ የሚያስገኘው ውጤት የተበደረውን ገንዘብም ሆነ የራሱን ካፒታል የተሻለ ደረጃ ላይ ሊያደርስ የሚያስችል መሆኑን በማረጋገጥ ለአበዳሪው የሚያቀርበው ጥናታዊ ሰነድ ነው፣

21. **“የብድር ትንተና”** ማለት የህብረት ስራ ማህበሩን የብድር አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ለብድር ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች ለምሳሌ የብድሩ መጠን፣ የክፍያ ጊዜ፣ ብድሩ የሚውልበት የስራ ዘርፍ፣ ለብድሩ የተያዘ ዋስትና፣ የብድሩ ያለመመለስ አደጋና ሌሎች ተዛማጅ ሁኔታዎች ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልክ በዝርዝር የሚጠናበትና ለውሳኔ የሚቀርብበት አሰራር ነው፣

22. **“አግባብ ያለው ባለስልጣን”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረት ሥራ

ኤጀንሲ ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ የተዋቀረ የህብረት ሥራ ጽ/ቤት ነው፤ ፣

23. **"የፋይናንስ ግብይት ትስስር" ማለት** የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን የብድር ፍላጎት ለማሟላት የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥም አቅም ካላቸው አበዳሪ ተቋማት ጋር የሚደረግ ትስስር ነው፡፡

24. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል ፡፡

3. የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ ስር በተደራጁ የቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4. የመመሪያው ዓላማ

1. ኅብረት ስራ ማህበራት ለአባላቶቻቸው ፍትሃዊና ተደራሽ የብድር አገልግሎት መስጠት ለማስቻል፣
2. በኅብረት ስራ ማህበራት የሚሰጡ የብድር አገልግሎቶች ህግና ስርዓትን ተከትለው ተፈፃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል፣

5. የቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት የብድር አገልግሎት ዓላማ

1 አባላት ያለባቸውን የገንዘብ እጥረት በመፍታትና የመስራት አቅማቸውን በማጐልበት የአባሎቻቸውን ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ቋሚና ዘላቂ በሆነ መንገድ መፍታት እንዲችሉ ማገዝ፣

2 በህብረት ስራ ማህበራት □ስዓ □ዙለ□□ የብድር ዓይነቶችን ተግባራዊ በማድረግ ለአባላት የብድር አገልግሎት በስፋት ማቅረብ፣

3 የብድር አጠቃቀም ልምድና ባህል ማዳበር፣

4 ለአባላት የብድር አገልግሎት በመስጠት አባላት ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ በማሳደግ የአባላትን ገቢ አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ፣

ክፍል ሁለት

የብድር ኮሚቴ ወይም ባለሙያ አወቃቀር፤ተግባርና ሃላፊነት

6. የብድር ኮሚቴ አወቃቀር

1. የብድር ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ ከ3-5 አባላት ያሉት ሆነው ተጠሪነታቸውም ለስራ አመራር ኮሚቴ ይሆናል፣
2. የህብረት ስራ ማህበራት የብድር ኮሚቴ ሰብሳቢ ፣ፀሐፊና አባል ይኖሩታል፣
3. ማንኛውም የብድር ኮሚቴ የአገልግሎት ዘመኑን ሲጨርስ ከኃላፊነት ይነሳል፡፡ ሆኖም አባሉ በራሱ ፈቃድ ወይም ኃላፊነቱን በአግባቡ ባለመወጣቱ ምክንያት የአገልግሎት ዘመኑን ሳይጨርስ በማንኛውም ጊዜ ከኃላፊነቱ ሊነሳ ይችላል፡፡

7. የብድር ባለሙያ

1. ኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አገልግሎት በተቀላጠፈ ሁኔታ ለአባላት መስጠት እንዲያስችለው

እንደስራዉ ስፋት እያየ የብድር ባለሙያ ሊቀጥር ይችላል፣

2. የብድር ባለሙያ አቀጣጠር ወይም የብድር ክፍል በኅብረት ሥራ ማህበሩ የውስጥ የሰው ሃብት አስተዳደርና አደረጃጀት መመሪያ መሰረት ይሆናል፣

8. የብድር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የኅብረት ስራ ማህበሩን የብድር አስተዳደር መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል፣
2. □ኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓመታዊ የብድር ፍላጎት መጠን ያዘጋጃል፣
3. የኅብረት ስራ ማህበሩ በበጀት ዓመቱ የሚያስራጨው ብድር በጠቅላላ ጉባዔ የፀደቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣ በስራ አመራር ኮሚቴ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፣
4. የኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር አገልግሎት የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን ያረጋግጣል፣

5 ለኅብረት ስራ ማህበሩ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎች በብድር አስተዳደር መመሪያና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፣

6 ብድር ጠያቂው ለሚጠይቀው ብድር በቂ ዋስትና ማቅረቡንና አስፈላጊ የብድር ሰነዶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣

7 ብድር ከመጠየቁ በፊት ለብድር አገልግሎት የተመደበ ገንዘብ መኖሩን ያረጋግጣል፣

8 ኮሚቴው ውሳኔውንና የአመልካቹን የግል ሁኔታዎች በሚስጥር መያዝ አለበት፣

9 ኮሚቴው የቀረበልትን የብድር ጥያቄ መርምሮ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለስራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣

10 የተሰጠ ብድር ለተጠየቀበት አላማ መዋሉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

11 የተሰጠ ብድር በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ እንዲመለስ ያደርጋል፣ በወቅቱ ያልተመለሰ ብድርን ያልተመለሰበትን

ምክንያት ያጣራል፣ ውጤቱን ለስራ አመራር ኮሚቴ በሪፖርት ያሳውቃል፣

12 የብድር መክፈያ ጊዜ ማራዘሚያና ተጨማሪ ብድር የተጠየቀበትን ማመልከቻ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለስራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣

13 አዳዲስ የብድር አሰራር ሃሳብ ያፈልቃል፣ለስራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

14 የብድር አስተዳደር መመሪያ እንዲሻሻል ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፣

15 ስለ ብድር የስራ እንቅስቃሴ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ለስራ አመራሩ ሪፖርት ያቀርባል፣

16 የብድር ኮሚቴ ያካበተውን ልምድ ለተተኪ የኮሚቴ አባል ወይም የብድር ባለሙያ የማስተማርና ልምዱን የማካፈል ኃላፊነት አለበት፣

17 የተለያዩ ሠነዶችና ቅፃቅፆች በማዘጋጀት እና የብድር ማሰባሰቢያ የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት በየጊዜው ተበዳሪዎች እንዲያውቁት ያደርጋል፣

18 ኅብረት ስራ ማህበሩ ስለሚሰጠው የተለያዩ የብድር አይነቶች ግንዛቤ ይፈጥራል፣

19 ለአባላት የብድር አጠቃቀም ላይ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

20 ሌሎች ተጨማሪ ብድር ነክ የሆኑ ስራዎችን በህብረት ስራ ማህበሩ የስራ አመራር ኮሚቴ ሲሰጥ ይተገብራል፡፡

9. የብድር ባለሙያ ተግባርና ሃላፊነት

የብድር ባለሙያ ቀጥረው በሚያሰሩ የኅብረት ስራ ማህበራት ከዚህ የሚከተሉትን ተግባራት በማከናወን ለብድር ኮሚቴው ወይም ለቅርብ ሃላፊ ያቀርባል፡፡

1. የኅብረት ስራ ማህበሩን የብድር አስተዳደር መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል፣

2. □ኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓመታዊ የብድር ፍላጎት መጠን ያዘጋጃል፣
3. የኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር አገልግሎት የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን ያረጋግጣል፣
4. ለኅብረት ስራ ማህበሩ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎች በብድር አስተዳደር መመሪያና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፣
5. ብድር ጠያቂው ለሚጠይቀው ብድር በቂ ዋስትና ማቅረቡንና አስፈላጊ የብድር ሰነዶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣
6. ብድር ከመጠየቁ በፊት ለብድር አገልግሎት የተመደበ ገንዘብ መኖሩን ያረጋግጣል፣
7. ባለሙያው ውሳኔውንና የአመልካቹን የግል ሁኔታዎች በሚስጥር መያዝ አለበት፣

8. የቀረበለትን የብድር ጥያቄ መርምሮ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለቅርብ ሃላፊ ያቀርባል፣

9. የተሰጠ ብድር ለተጠየቀበት አላማ መዋሉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

10. የተሰጠ ብድር በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ እንዲመለስ ያደርጋል፣ በወቅቱ ያልተመለሰ ብድርን ያልተመለሰበትን ምክንያት ያጣራል፣ ውጤቱን ለቅርብ ሃላፊ በሪፖርት ያሳውቃል፣

11. የብድር መክፈያ ጊዜ ማራዘሚያና ተጨማሪ ብድር የተጠየቀበትን ማመልከቻ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለቅርብ ሃላፊ ያቀርባል፣

12. አዳዲስ የብድር አሰራር ሃሳብ ያፈልቃል፣ለቅርብ ሃላፊ ያቀርባል፣

13. የብድር አስተዳደር መመሪያ እንዲሻሻል ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፣

14. ስለ ብድር የስራ እንቅስቃሴ ወቅታዊ ሪፖርት ለቅርብ ሃላፊ ያቀርባል፣
15. የተለያዩ ሠነዶችና ቅፃቅፆች በማዘጋጀት እና የብድር ማሰባሰቢያ የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት በየጊዜው ተበዳሪዎች እንዲያውቁት ያደርጋል፣
16. ህብረት ስራ ማህበሩ ስለሚሰጠው የተለያዩ የብድር አይነቶች ግንዛቤ ይፈጥራል፣
17. ለአባላት የብድር አጠቃቀም ላይ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
18. ሌሎች ተጨማሪ ስራዎችን በህብረት ስራ ማህበሩ የቅርብ ኃላፊ ሲሰጥ ይተገብራል፡፡

10. <u>የቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት የብድር አገልግሎት ተግባር</u>

1. የአባላትን የብድር ጥያቄ በወቅቱ ማስተናገድ፣

2. የብድር አገልግሎቱን ለማግኘት ብድር ፈላጊዎች ማሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች ቀድመው እንዲያውቁ ማድረግ፣

3. የብድር አጠቃቀምን በተመለከተ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

4. የተሰጠው ብድር ከነወለዱ በወቅቱ እንዲመለስ ክትትል ማድረግ፣

5. ስለ ብድር አስተዳድር ለአባላት፣ ለአቻ ማኅበራት እና ለኅብረተሰቡ ትምህርት፣ ስልጠናና መረጃ መስጠት፣

6. ገቢ የሚያስገኙ አማራጮችን በማጥናት፣ በማስጠናት፣ የቀረቡትን በመገምገም፣ ወዘተ... የአባላትን የመዋለ ንዋይ አቅም ማሳደግ፣

7. የአባላትን የብድር ፍላጎት ቀድሞ በማጥናትና በመለዬት ከህብረት ስራ ማህበራት ሃብት በላይ የሆነውን የብድር ፍላጐት ለማሟላት

አዋጭነቱን በማረጋገጥ ከህጋዊ አበዳሪ አካላት ብድር በማፈላላግ ለአባላት ማቅረብ ፡፡

11. የብድር ኮሚቴ ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 8 የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባቡ ባለመወጣት በኅብረት ስራ ማህበሩ ላይ በሚደርሰው ጉዳትና ኪሳራ የኮሚቴ አባላት በግልም ሆነ በጋራ በማንኛውም ጊዜ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

12. <u>የብድር ባለሙያ ተጠያቂነት</u>

የብድር ባለሙያው የኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር አስተዳደር መመሪያ ከሚፈቅደው አሰራር ውጪ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ለሚፈፅመው ጥፋት፣ ለሚደርሰው ጉዳትና ኪሳራ በህብረት ስራ ማህበራት የሰራተኞች የሰው ሃብት አስተዳደር መመሪያና በህግ አግባብ ተጠያቂ ይሆናል፣

ክፍል ሦስት

የብድር አይነቶች፤ስለብድር ወለድ፤የብድር ማመልከቻና ፍቃድ

13. የብድር አይነቶች

ሀ/ በቆ□

1. የአጭር ጊዜ ብድር፦ ማለት የመመለሻ ጊዜው እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ ብድር ነው፣
2. የመካከለኛ ጊዜ ብድር፦ ማለት የመመለሻ ጊዜው እስከ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ ብድር ነው፣
3. የረጅም ጊዜ፦ ማለት የመመለሻ ጊዜው እስከ አስር ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ ብድር ነው፣

ለ/ በስራ ዘርፍ

1. ለገቢ ማስገኛ
2. ለቋሚ ንብረትና ለተለያዩ ግዥዎች፣
3. ለቤት ግንባታና ዕድሳት
4. ለማህበራዊ አገልግሎት
5. ለስራ ማስኬጃ

14. ወለድ የሚከፈልባቸው የብድር አገልግሎት

1. ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ወለድ የሚያስከፍልባቸውን የብድር አግልግሎት ይሰጣል፣
2. ኅብረት ሥራ ማኅበሩ የወለድ መጠን ጣሪያ በመተዳደሪያ ደንቡ የሚያስቀምጥ ሲሆን የስራ አመራር ኮሜቴ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አጥንቶ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ በማጸደቅ የወለድ ጣሪያ ሊስተካከል ይችላል፣
3. ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ለሰጠው ብድር የሚሰበሰበው የወለድ መጠን በጠቅላለ ጉባኤ በጽደቀው የወለድ መጠን መስረት ይሆናል፡፡

4. ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ወለድ ለሚያስገኝ የብድር አገልግሎት የሚሆን አሰራር ይዘረጋል፣ ለሚሰጣቸው ብድሮች የተለያየ የወለድ ምጣኔዎች አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፣

5. ኅብረት ሥራ ማኅበሩ በወለድ የተሰጠ ብድር የሚሰበሰብ ሂሳብ መግባት ያለበት ወለድ በሚያስገኝ የሂሳብ ቁጥር ውስጥ ነው፣

15. <u>የወለድ አልባ የብድር አገልግሎቶች</u>

1. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ወለድ አልባ የሆኑ የብድር አገልግሎት ለአባሎቻቸው ሊሰጡ ይችላሉ፣ ለሚሰጡት ብድር ምንም አይነት ወለድ አያስከፍሉም ወይም አይቀበሉም፣

2. የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚሰጡት የወለድ አልባ ብድር አገልግሎቶች እንደ ኅብረት ሥራ ማኅበራት አቅምና ባህሪ የተለያዩ የወለድ አልባ የብድር አገልግሎቶችን

እያጠና በብድር አስተዳደር መመሪያ ውስጥ በማካተት በጠቅላላ ጉባኤ አጸድቆ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተሉት የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎቶች ለአባላቶቻቸው ይሰጣሉ፣

1. ሙራበሃ፣
2. ሰለም ፣
3. ኢጃራ
4. ሙሻራክ ወዘተ ፣

3. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ከላይ የተጠቀሱትን ሸሪዓ መር የፋይናንስ አገልግሎት ለብድር አስተዳደር አመቺ የሚሆኑ አሰራሮች፣ ሰነዶች፣ መዛግብቶች እና ቅፃቅፆችን ያዘጋጃል፡፡

4. የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት መሰረት የሚያደርገው ግዥና ሽያጭን ሲሆን ኅብረት ሥራ ማኅበሩ በአባላት ጥያቄ መነሻ መሰረት የገዛውን እቃ የራሱን ወጪ መሸፈኛ ጨምሮ

ለአባሉ መልሶ በመሸጥ ላይ የተመሰረተ ነው፤ ዝርዝር አሰራሩ በብድር አስተዳደር መመሪያ ይገለጻል፤

5. የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት የሚሰጠው ከወለድ አልባ ከተሰበሰበ ቁጠባ ብቻ ይሆናል፤

6. በምንም ሁኔታ ወለድ የሚታሰብባቸው ገንዘቦች ለወለድ አልባ አገልግሎት አይውሉም፤

7. ከወለድ አልባ የሚሰበሰብ ብድር ገቢ የሚሆነው በወለድ አልባ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ ነው፤

16. የብድር ጣሪያ አወሳሰን

1. ማንኛውም የኅብረት ስራ ማኀበር የሚሰጠውን ብድር ለአባላት ተደራሽ ለማድረግ የህብረት ስራ ማህበራትን ሀብት ያገናዘበ የብድር ጣሪያ በመተዳደሪያ ደንቡ ወስኖ ያስቀምጣል፤ የብድር ጣሪያውም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ

በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ሊሻሻል ይችላል፡፡

2. አንድ አባል ሊበደር የሚችለው ከፍተኛ የብድር ጣሪያ ኀብረት ስራ ማህበሩ በየዓመቱ የሚመድበው የብድር ገንዘብ መጠን ለብድር ጠያቂዎች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ እንዲሆን መደረግ አለበት ፡፡
3. በአንቀፅ 16.1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚፈቀደው የብድር መጠን ተበዳሪው በሚያቀርበው ዋስትና መሰረት ይሆናል፤
4. አንድ ተበዳሪ ብድር ማግኘት የሚችለው ከኀብረት ስራ ማህበሩ ውስጥ በሚኖረው ተሳትፎ መሰረት ይሆናል ፡፡
5. የብድር ጣሪያ መጠን ሊሻሻል የሚችለው ከኀብረት ስራ ማህበሩ አባላት ውስጥ 2/3ኛው በተገኙበት ሲወሰንና አግባብ ባለው ባለስልጣን ሲፀድቅ ነው፡፡

17. የብድር ወለድ

1. የኅብረት ስራ ማህበሩ ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት ተመጣጣኝ ወለድ ያስከፍላል፡፡ ነገር ግን የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት ለመስጠት ከወሰኑ የብድር ወለድ አያስከፍሉም፣
2. የኅብረት ስራ ማህበሩ በጊዜና በዘርፍ ለሚሰጠው የተለያየ የብድር ዓይነት የተለያየ ዓይነት የወለድ ተመን ይኖረዋል፡፡ ይህንንም በብድር አስተዳደር መመሪያ ላይ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርበታል፣
3. የብድር ወለድ በብድር ኮሚቴ ወይም በብድር ባለሙያ አማካኝነት እየተጠና በስራ አመራር ኮሚቴ ከታዬ በኋላ በጠቅላላ ጉባዔ ሲፀድቅ ስራ ላይ ይውላል፣
4. በብሔራዊ ባንክ የሚደረግ የወለድ ለውጥን ተክትሎ የኅብረት ስራ

ማህበራት የብድር ወለድ መጠን ለውጥ ያደርጋሉ፣

5. የኅብረት ስራ ማህበራት የብድር ወለድ ተመን ለማውጣት የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፣

ሀ/ ለብድር የሚውል ገንዘብ የሚያስከትለው ዋጋ

ለ/ ብድሩን ለማስፈፀም የሚደረግ አስተዳደራዊ ወጪ

ሐ/ ለማይመለሱ ብድሮች መጠባበቂያ

መ/ በወቅቱ የገንዘብ የመግዛት አቅም

ሠ/ የኅብረት ስራ ማህበሩ ማግኘት ያለበት ተመጣጣኝ ትርፍ

6. የብድር ወለድ መታሰብ የሚጀምረው ተበዳሪው ገንዘቡን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣

7. የኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር ወለድ መጠን ለውጥ ሲያደርግ በለውጡ

መሰረት ቀደም ሲል የተበደሩትም ሆነ አዲስ ተበዳሪዎች ላይ የብድር ወለድ ማስተካከያ ይደረግባቸዋል፣

8. የኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር ወለድ ለውጡን ለተበዳሪዎች በጹሑፍ ወይም በማስታወቂያ ያሳውቃል ፣
9. □ኅብረት ሥራ ማህበሩ በብድር ውሉ መሰረት ከተበዳሪዎች ወለድና ዋና ገንዘብ ይሰበስባሉ፣

18. የብድር ማመልከቻ አቀራረብ

1. አባላት ኅብረት ስራ ማህበራት በሚያዘጋጁት የብድር ማመልከቻ ቅፅ መሰረት ሞልተውና ፈርመው ለስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ለስራ አስኪያጅ ያቀርባሉ፣
2. ማመልከቻው የቀረበለት አካል ማመልከቻውን መዝግቦ ለብድር ኮሚቴው ወይም ለብድር ባለሙያው ይመራል፣

3. የብድር ኮሚቴው ወይም የብድር ባለሙያው የተመራለትን የብድር ማመልከቻ በቅደም ተከተል ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ተራው እንዲጠበቅና እንዲስተናገድ ያደርጋል፣

4. ተበዳሪው ከብድር ማመልከቻ ጋር የሚከተሉት በማስረጃነት መታየትና መቅረብ አለባቸው

ሀ/ በቁጠባ ያለ ገንዘብ

ለ/ የዕጣ መጠን

ሐ/ ለተበዳሪው ዋስ የሆኑ አባላት የቁጠባና የዕጣ መጠን

መ/ የተበዳሪው ዋስትናና የዋስትና ማረጋገጫ

ሠ/ የተበዳሪው የስራ ዕቅድና

ረ/ ተበዳሪው ዋስ የሆነበት ብድር ካለ የብድሩ መጠንና ያለበት ሁኔታ

ሰ/ ተበዳሪው ከህብረት ስራ ማህበሩ ተበድሮ ከሆነ የብድር

መጠን፣የተበደረበት ጊዜ፣የተከፈለና ያልተከፈለ ብድር መጠን፣

ሸ/ ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች

5. የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ በአመልካቹ በቀረበው የብድር ማመልከቻ መነሻ መሰረት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ መጠይቅ ሊያደርግ ይችላል፤

   1. ተበዳሪው የጠየቀው ብድር ሊያውለው ከፈለገው የስራ መስክ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለማወቅ፣
   2. ተበዳሪው ብድሩን ከመውሰዱ በፊት ስለገንዘብ አጠቃቀም ተጨማሪ ግንዛቤ እንዳለው ለማወቅ፣

3. አመልካቹ ያቀረበው የብድር ጥያቄና የሞላውን ማመልከቻ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ፣
4. በቀረበው ማመልከቻ ላይ ያልተብራሩና ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮችን ግልፅ ለማድረግና በቂ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ፣
5. በተበዳሪው የሚቀርበው ዋስትና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ፣

6. መጠይቁ ከአባሉ የብድር ማመልከቻ ጋር በአባሪነት ተያይዞ መቀመጥ ይኖርበታል፣
7. የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያው የቀረበለትን የብድር ማመልከቻ መርምሮ ለስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ለስራ አስኪያጅ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
8. ከማመልከቻ አቀራረብ እስከ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ በየሂደቱ የሚወስደውን ጊዜ ህብረት ስራ ማህበራት በብድር

አስተዳደር መመሪያቸው ውስጥ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፣

9. ብድር የሚጠይቁት የኅብረት ስራ ማህበራት ከሆኑ ከሚቀርበው የብድር ማመልከቻ ጋር የህብረት ስራ ማህበሩን አቋም የሚገልፅ የ3 ተከታታይ አመታት የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት፣ የስራ ዕቅድና የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

19. <u>የብድር አፈቃቀድና ትንተና</u>

1. የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያው የሚቀርብለትን የብድር ጥያቄ ከመወሰኑ በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን አለበት፡-

ሀ/ ተበዳሪው አባል የኅብረት ስራ ማህበሩን ህግና ደንብ አክባሪ መሆኑን፣

ለ/ ተበዳሪው ብድሩን ለመጠቀም የፈለገበት ስራ ተበዳሪው ከተሰማራበት ስራ

ጋር ያለው ዝምድናና አባሉ ስራውን የመፈፀም ብቃት፣

ሐ/ ተበዳሪው በቋሚና በተንቀሳቃሽ ያለው ንብረት፣ ካቀደው ስራ ጋር ያለው ተያያዥነትና ተዛማጅነት፣

መ/ ተበዳሪው የሚያቀርበው ዋስትና ከሚፈለገው የዋስትና መጠን ጋር ያለው ተመጣጣኝነት፣

ሠ/ የተረጋጋ የስራ ሁኔታ መኖሩ፣

ረ/ የአባሉ ቀደም ባሉ ብድሮች አወሳሰድና አመላለስ ላይ ያለው አፈፃፀም፣

ሰ/ ተበዳሪው የኅብረት ስራ ማህበር ከሆነ አግባብ ባለው ባለስልጣን ለሶስት ተከታታይ ጊዜያት የተደረገ ጤናማ የሂሳብ ምርመራ ውጤት፣

2. ማንኛውም ብድር ከመሰጠቱ በፊት የአበዳሪውን የኅብረት ስራ ማህበር የፋይናንስ ሁኔታ የሚገልፅ፡-

ሀ/ ለብድር የዋለ

ለ/ በቁጠባ የተቀመጠ

ሐ/ ከብድር የተሰበሰበ

መ/ ያልተሰበሰበ ብድር

ሠ/ ሊሰበሰብ የሚችል የመክፈያ ጊዜው ያለፈበት ብድርሊሰበሰብ የማይችል የብድር መጠን፣ የሚገልፅ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ከቀረበ በኋላና ማህበሩ ጤናማ የፋይናንስ አቋም ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ብድሩ መስጠት አለበት፡፡

3. ብድር ጠያቂው በአንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 19.1 የተጠቀሱትን የማያሟላ ከሆነ ብድር አይፈቀድለትም፣

4. ኅብረት ስራ ማህበሩ የቀረበውን የብድር ጥያቄ ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን

ምክንያት በዝርዝር በመግለፅ ለአመልካች በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ያሳውቃል፣

5. ብድር ጠያቂው ብድር የተከለከለበት ምክንያት ከደንቡና ከብድር መመሪያው ውጪ የተፈፀመ ነው ብሎ ካመነ ለኅብረት ስራ ማህበሩ የስራ አመራር ኮሚቴ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፣ የስራ አመራር ኮሚቴው በ7 የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፣

6. በውሳኔው ያልረካ አመልካች በኅብረት ስራ ማህበሩ በተዘረጉ የክርክር አወሳሰን ሂደቶችና አግባብ ባለው ህግ መሰረት ማቅረብ ይችላል።

7. የኅብረት ስራ ማህበራት ብድር ጠያቂውን ለመገምገም የሚስችል የብድር ጠያቂ መገምገሚያ ቅፅ ያዘጋጃሉ፣ የቅፁ ይዘትም የሚከተሉት ነጥቦች መያዝ ይኖርበታል፡

    ሀ/ የማመልከቻው ቁጥርና ቀን

    ለ/ አጠቃላይ የተበዳሪው ሁኔታ

ሐ/ የተበዳሪው አቅም

መ/ ተበዳሪው ዕቅዱን ለመፈፀም ያለው ብቃት

ሠ/ የተበዳሪው ዋስትና ሁኔታ

ረ/ የስራ አካባቢው ሁኔታ፣

ሰ/ የተበዳሪው የብድር አመላለስ ሁኔታ፣

ሸ/ የተጠየቀው የብድር ሁኔታ

ቀ/ የውሳኔ ሃሳብ

በዚህ መሰረት የስራ አመራር ኮሚቴ የቀረበለትን የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ ውሳኔ መርምሮ ያፀድቀዋል፡፡ ሆኖም በኅብረት ስራ ማህበሩ ስራ አስኪያጅ ሊፀድቁ የሚችሉ ብድሮችን በኅብረት ስራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የስራ አመራር ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

20. <u>ብድር የሚከለከልባቸው ምክንያቶች</u>

1. በዕቅድና በዓላማ ላይ ያልተመሠረተ የብድር ጥያቄ ሲቀርብ፣

2. ከኅብረት ስራ ማህበሩ የወሰደውን ብድር ያለበቂ ምክንያት ክፍያ አቋርጦ በግፊት እንዲከፍል የተደረገና ጥሩ ያልሆነ የብድር ታሪክ ያለው ተበዳሪ ሲሆን ፣

3. የመክፈል አቅሙና ፈቃደኝነት፣ የካፒታል አቅሙ ውስን የሆነና ተበዳሪው ያለበት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የገበያ ተወዳዳሪነት እና ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች ብድር ለመመለስ እንቅፋት ይሆናል ተብሎ ሲታመን፣

4. ዋስትና ማቅረብ የማይችል ከሆነ፣

5. ተበዳሪው ከሌላ አበዳሪ አካል ላለበት ብድር መክፈያ አገልግሎት የሚያውለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

6. በኅብረት ስራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተቀመጡ

ግዴታዎችን በአግባቡ የማይወጣ ከሆነ

7. በኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር አመላለስ መልካም ሪከርድ የሌለው አባል ከሆነ፣

8. ተበዳሪው ወይም ዋሱ ለሌላ አባል ዋስ ሆኖ የዋስትናው መጠን ወይም ቀሪው ዕዳ ከፍተኛ ከሆነ፣

ክፍል አራት

የብድር ዋስትና እና ዉል

21. የብድር ዋስትና

1. የኅብረት ስራ ማህበራት ብድር በመስጠት ሊደርስ የሚችለውን ያልተጠበቀ ችግር መከላከል አለባቸው፣
2. ኅብረት ስራ ማህበራት ለሚያበድሩት ብድር የዋስትና ማሲያዣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሊያካትት ይችላል፡-

ሀ/ የተበዳሪውንና የዋሱን ቁጠባና ዕጣ

ለ/ ቋሚ ንብረት

ሐ/ የቋሚ ሰራተኛ ደመወዝ

መ/ ቦንድ

3. ተበዳሪው ለሚበደረው ገንዘብ ዋናውን፣ ወለዱንና ሌሎች ወጭዎችን ጨምሮ ለመክፍ የሚችል ዋስትና ማቅረብ አለበት፣

4. ተበዳሪው ካለው የመደበኛ ቁጠባ መጠን በላይ ብድር የሚፈልግ ከሆነ ለዚሁ ተጨማሪ ለሆነው ገንዘብ የሚከተሉትን በዋስትናነት ለኅብረት ስራ ማህበሩ ማቅረብ ይችላል፣

ሀ/ የኅብረት ስራ ማህበሩ አባል የሆነ እና ለዋስትና በቂ የሆነ ቁጠባና ዕጣ ያለው፣

ለ/ የባለቤትነት ማረጋገጫ

የሚቀርብበት ቋሚ ንብረት

ሐ/ በህግ ተቀባይነት ያላቸውና

ወደ ገንዘብ ሊለወጡ የሚችሉ

በመያዣነት መቅረብ

የሚችሉ ሰነዶች፣

መ/ በኅብረት ስራ ማህበሩ

ውስጥ በተለያየ ሁኔታ የተጠራቀም

ገንዘብ፣

5. ብድር ጠያቂው በተለያየ ምክንያት የሚፈለግበትን ዕዳ መክፈል ባይችል የኅብረት ስራ ማህበሩ አባሉ ካለው የመደበኛ ቁጠባ፣ የዕጣና ሌሎች የአባሉን ድርሻ ለዕዳ ማካካሻ ማዋል ይችላል፣

6. ተበዳሪው ዕዳውን መክፈል ካልቻለ የዋሱ/የዋሶች ቁጠባና ዕጣው ለዕዳው ማካካሻ ይውላል፣

7. ማንኛውም የኅብረት ስራ ማህበር ለሚያቀርበው የብድር አገልግሎት

በዋስትና የሚይዘውን ንብረት ወይም ገንዘብ ዕዳው በወቅቱ ካልተከፈለ ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በመሸጥ ወይም ገንዘቡን ለዕዳ ማካካሻነት በማዋል ዕዳውን የማስከፈል መብት አለው፡፡

8. የቋሚ የንብረቱ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ግምት በህጋዊ ተቋም በማስገመት የንብረቱን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ በዋስትናነት በመያዝ የቋሚ ንብረቱን ግምት እስከ 70% ብድር ሊሰጥ ይችላል፡፡

9. ለደመወዝ ዋስትና የሚቀርብ የዋስትና መጠን የዋሱ ደመወዝ 1/3ኛው ተበዳሪው በብድር ዘመኑ ውስጥ በየወሩ የሚከፈለውን የዕዳ ክፍያ መጠን የሚሸፍን መሆን መቻል አለበት፣

10. የብድር ጣሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ አባል የቁጠባውን 95 በመቶ ድረስ ያለ ተጨማሪ ዋስትና ሊበደር ይችላል፣ ሆኖም ብድሩ ከተጠቀሰው መጠን በላይ ከሆነ አባሉ ለተጨማሪው ብድር መጠን ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል፣

11. ዋስትና ሊወርድ ወይም ሊቀየር የሚችለው በቀሪው የዕዳ መጠን ተተኪ ዋስትና ሲቀርብና ውሉ እንደ አዲስ ሲፈረም ወይም ብድሩ ሲጠናቀቅ ብቻ ነው፣

12. አንድ አባል ቁጠባውንና ዕጣ ለሌላ አባል በዋስትናነት ሊያስዝ ይችላል፣

13. ተበዳሪው የከፈለው የብድር ተመላሽ ገንዘብ መጠንና ቀሪው ዕዳ በተበዳሪው ዋስትና የሚሸፈን መሆኑን የኅብረት ስራ ማህበሩ

ካረጋገጠ ብድሩ ተከፍሎ ሳያልቅ ዋሶች ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ፣

14. ለሌላ ተበዳሪ ዋስ የሆነ ብድር ጠያቂ በአንቀፅ 20.3 በተቀመጠው መሰረት ዋስትና በማቅረብ መበደር ይችላል፣

15. ከላይ ለተዘረዘሩት የብድር ዋስትና አይነቶች የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

ሀ/ የቤት ካርታ እና የተሽከርካሪ የባለቤትነት ማረጋገጫና ከዕዳ ነፃ መሆኑን የሚገልፅ ሰነድ ከሚመለከተው አካል ማቅረብ፣

ለ/ በዋስትና የሚቀርበው ተሽከርካሪ ከሆነ ሙሉ ዋስትና መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ያለው ሆኖ ተበዳሪው ብድሩን

ሲወስድ ከኢንሹራንስ ጋር ያለው ውል በአበዳሪውና በተበዳሪው ስም እንዲቀየር የሚደረግ መሆን ይኖርበታል፣

ሐ/ የትዳር ጓደኛ ስምምነት የሚያሳይ ሰነድ፣ ካላገባ ማስረጃ የሚያቀርብ፣

መ/ የደመወዝ ዋስትና ከሆነ ከቀጣሪ መስሪያ ቤቱ ስለግለሰቡ የደመወዝ መጠን፣ጡረታ የሚወጣበት ጊዜ፣ድርጅቱን ሲለቁ በፅሁፍ ማሳወቅ የሚችል መሆኑን የሚያሳይ ደብዳቤ፣የብድሩን ክፍያ ከደመወዙ እየቆረጠ ለኅብረት ስራ ማህበሩ ለመክፈል መስማማቱን

በፅሁፍ ማረጋገጡ፣ተበዳሪው ብድሩን ካልከፈለ ዋሱ ከደመወዙ እየተቆረጠ ለኅብረት ስራ ማህበሩ ለመክፈል ስለመስማማቱና ግዴታ ስለመግባቱ በውል ሰነዱ ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፣

22. የብድር ውል

1. ኅብረት ስራ ማህበራት ለአባላት ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት በህግ ፊት ተቀባይነት ያለው የብድር ውል በማዘጋጀት ውል ይይዛሉ፣
2. ተበዳሪውና ዋሱ ከኅብረት ስራ ማህበሩ ጋር ታዛቢዎች(እማኞች) ባሉበት በአካል ቀርበው ይፈርማሉ፣
3. የብድር ውሉ፤ብድሩ የሚውልበት ዓላማ፣ የብድር መጠን፣ የወለድ መጠን፣የዋስትና ሁኔታና መጠን፣

የብድር ገንዘብ አፈቃቀድ፣ የብድር አመላለስ፣ግዴታዎችና ኃላፊነቶች፣ ውሉ የሚፀናበት ሁኔታ፣ የተበዳሪውንና የዋሱን ስምና ፊርማ፣የተበዳሪና የዋስ ባለቤት ስምና ፊርማ፣ የአበዳሪው ስምና ፊርማ፣ የእማኞች ስም አድራሻና ፊርማ፣በግልፅ ማመልከት አለበት፣

4. የብድር ውል ከተያዘ በኋላ ክፍያው በብድር ውሉ መሰረት ይፈፀማል፣
5. የብድር ውሉ ከተበዳሪው ማመልከቻ፣ ከብድር ኮሚቴ ወይም ከብድር ባለሙያው የውሳኔ ሃሳብ እና በሚመለከተው አካል ከፀደቀ ውሳኔ ጋር ተያይዞ በኅብረት ስራ ማህበሩ ጽ/ቤት መቀመጥ አለበት፣ በምንም አይነት ሁኔታ ከኅብረት ስራ ማህበሩ ጽ/ቤት የብድር ውሉ መውጣት የለበትም፣

6. ውሉ በበቂ ቅጂ ተዘጋጅቶ ለአበዳሪው፣ ለተበዳሪውና ለዋሱ/ዋሶች/ አንድ የውል ቅጅ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

23. የብድር ገንዘብ ስለመልቀቅ

1. ለተበዳሪዎች የተፈቀደውን የብድር ገንዘብ በአንድ ጊዜ ወይም በየምዕራፉ መክፈል ይቻላል፣
2. የኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር ውሳኔዎችና ውሉ ተሟልቶ በቀረበለት ከ3 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ብድሩን ለተበዳሪው የመልቀቅ ግዴታ አለበት፣
3. የኅብረት ስራ ማህበሩ ለተበዳሪው ክፍያ የሚፈፀመው በቼክ ወይም በተበዳሪው የሂሳብ ቁጥር ገቢ የሚሆን ይሆናል፣
4. ብድሩ በየምዕራፉ ለተበዳሪው የሚከፈል ከሆነ የሚቀጥለው ብድር ከመሰጠቱ በፊት ተበዳሪው ቀደም ብሎ በየምዕራፉ ለወሰደው ብድር አጠቃቀም ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣

5. ብድር የተፈቀደለት አባል በ5 ቀን ውስጥ ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ብድሩን ካልወሰደ ወይም ሌላ ስምምነት ካላደረገ ብድሩ ይሰረዛል፣
6. የብድር ክፍያው እንደተፈጸመ በኅብረት ስራ ማህበሩ የሒሳብ መዝገብና ሰነዶች ውስጥ ዕዳው መመዝገብ ይኖርበታል፣

ክፍል አምስት

የብድር አመላለስና የመክፈያ ግዜ

24. የብድር አመላለስ ስርዓት

የኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር አመላለስ ስርዓት የቀጥተኛ ወለድ ስሌት አሰራርን የሚከተል ሲሆን እንደ ኅብረት ስራ ማህበራት ውሳኔ ከሚከተሉት አንዱን ሊጠቀሙ ይችላሉ፤

1. በብድር ጊዜው መጨረሻ የመመለስ ስርዓት፡- ይህ ስርዓት ዋናው ብድር በብድሩ መጨረሻ ጊዜ የሚመለስ ሲሆን ወለዱ ግን በብድር ውሉ ውስጥ

በተወሰነው የክፍያ ጊዜ መሰረት ሳይቋረጥ ይከፈላል፣

2. በከፊል የመመለስ ስርዓት፦ የዚህ ዓይነት የአከፋፈል ስርዓት በህብረት ስራ ማህበሩና በተበዳሪው መካከል በሚደረገው ስምምነት መሰረት በየክፍያ ጊዜው የተወሰነውን ዋናና ወለድ ይከፍላል፣

3. እየቀነሰ የሚሄድ ሚዛን ወለድን በማስላት የመመለስ ስርዓት፦ በዚህ ዓይነት የአመላለስ ስርዓት ሁለት ዓይነት ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል፤

   ሀ/ የክፍያ መጠኑ እየቀነሰ የሚሄድ የአከፋፈል ስርዓት፦ በክፍያ ጊዜው የሚከፈለው የክፍያ መጠን እየቀነሰ የሚሄድ ሆኖ የሚከፈለው ዋና የብድር መጠን እኩል ሲሆን የወለድ መጠኑ ግን እየቀነሰ ይሄዳል፡፡

ለ/ የክፍያ መጠኑ እኩል የሚሆንበት የአከፋፈል ስርዓት፡- ይህ የአከፋፈል ስርዓት በየክፍያ ጊዜው የመከፈለው መጠን እኩል ሆኖ ዋናው እየጨመረ የሚሄድ ሲሆን የሚከፈለው የወለድ መጠን ግን በየክፍያ ጊዜው የሚከፈለውን የዋና ክፍያ መጠን ያህል እየቀነሰ ይሄዳል፡፡

25. <u>የብድር መክፈያ ጊዜና አሰባሰብ</u>

1. ተበዳሪው የተበደረውን ብድር በብድር ውሉ መሰረት ከፍሎ ማጠናቀቅ አለበት፣
2. ተበዳሪው በብድር ውሉ ከተቀመጠው የብድር መክፈያ ጊዜ በፊት ብድሩን ከፍሎ ማጠናቀቅ ይችላል፣
3. ተበዳሪው በገባው ውል መሰረት ብድሩንና ሌሎች ግዴታዎችን ለኅብረት ስራ ማህበሩ ገቢ ያደርጋል፣

4. የኅብረት ስራ ማህበሩ ብድር አሰባሰብን አስመልክቶ የመሰብሰቢያ ጊዜ ሰሌዳ ማውጣት አለበት፣
5. ብድሩ ገቢ ለማስገኘት ከሆነ እና ዕዳውን ለመክፈል የዝግጅት ጊዜ የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ በተበዳሪው ጥያቄ ለተበዳሪው የእፎይታ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ይህም በኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር አስተዳደር መመሪያ በግልፅ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡
6. ማንኛውም የእፎይታ ጊዜ በብድር ውል ዘመኑ የተካተተ ይሆናል፡፡
7. የብድር ዘመኑ የሚታሰበው በስምምነቱ መሰረት ተበዳሪው ውል ፈፅሞ የብድሩ ገንዘብ ክፍያ ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ ይሆናል፡፡
8. የኅብረት ስራ ማህበሩ የሚያወጣው የብድር አሰባሰብ ስርዓት እንደተጠበቀ ሆኖ ከተበዳሪው የተሰበሰበ የብድር

ገንዘብ በዕለቱ በኅብረት ስራ ማህበሩ የሂሳብ ቁጥር ገቢ መደረግ አለበት፣

9. ተበዳሪው የብድር ክፍያውን ካቋረጠ የብድር ኮሚቴው ወይም የብድር ባለሙያው የተቋረጠበትን ምክንያት ለማወቅ ተበዳሪውን በወቅቱ በመጥራት ምክንያቱን ማጣራትና ስለ ሁኔታው ለቅርብ ኃላፊው ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፣
10. ሪፖርት የቀረበለት ኃላፊ ከሪፖርቱ በመነሳት ተበዳሪው ክፍያውን የሚቀጥልበት ሁኔታ ያመቻቻል፤ ሆኖም ተበዳሪው ብድሩን ለመመለስ ፍቃደኛ ካልሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ እና በብድር አስተዳደር መመሪያው መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣
11. የኅብረት ስራ ማህበራት ተበዳሪዎች የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ አለማዋላቸውን ሲያረጋግጡ የብድር

መመለሻ ጊዜው ሳይደርስ ብድሩ እንዲመለስ ማድረግ ይችላሉ፣

12. ነገር ግን ተበዳሪዎች የተበደሩትን ብድር ለታለመበት ዓላማ ያላዋሉበት ምክንያት ዓሳማኝ ሆኖ ሲገኝና አዋጭ የሆነ ተለዋጭ ዕቅድ ማቅረብ ሲችሉ ብድሩ እንዲፀና ይደረጋል፡፡

26. <u>የብድር መክፍያ ጊዜን ስለማራዘም</u>

1. ተበዳሪው የብድር መክፈያ ጊዜ እንዲራዘምለት በማመልከቻ ሊጠይቅ ይችላል፣
2. የስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ስራ አስኪያጅ የቀረበውን የብድር መክፈያ ጊዜ የማራዘም ጥያቄ ለብድር ኮሚቴ ወይም ለብድር ባለሙያው አስተያየት እንዲሰጥበት ይመራል፣
3. የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያው የቀረበለትን የብድር መክፈያ ማራዘሚያ ጥያቄ ገምግሞ የውሳኔ ሃሳብ

ለስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ስራ አስኪያጅ ያቀርባል፣

4. የስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ስራ አስኪያጅ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቶ ውሳኔውን ለተበዳሪው ያሳውቃል፣

5. ቀደም ሲል የተገቡ ውሎች ወይም ግዴታዎች በብድር መክፈያ ጊዜ መራዘም ምክንያት በሌላ ውል መተካት አለባቸው፡፡

27. <u>የብድር መክፈያ ጊዜ ሊራዘም የሚችልበት ምክንያትና የጊዜ ገደብ</u>

1. ተበዳሪው ከአቅም በላይ የሆነ ተደራራቢ ችግር ሲያጋጥመውና ይህም በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ፣
2. ማንኛውም ብድር የመክፈያ ጊዜው ሊራዘም የሚችለው ቢያንስ የብድሩ 75 በመቶ የተከፈለ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

3. በአንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 26.1 እና 26.2 የተመለከቱት ሲሟሉ የማራዘሚያ ጊዜውም፡-

ሀ/ ለአጭር ጊዜ ብድር ከ3 ወር ያልበለጠ

ለ/ ለመካከለኛ ጊዜ ብድር ከ9 ወር ያልበለጠ

ሐ/ ለረጅም ጊዜ ብድር ከ18 ወር ያልበለጠ

28. <u>ተጨማሪ ብድር ስለመጠየቅ</u>

1. ተጨማሪ ብድር ጥያቄ ሲቀርብ የጥያቄው ተገቢነት ታይቶ ተጨማሪ ብድር ሊፈቀድ ይችላል፣
2. ተጨማሪ ብድር ጥያቄ አቀራረብና አፈቃቀድ በአንቀፅ 17 እና 18 መሰረት ይሆናል፣
3. ለሚቀርበው ተጨማሪ የብድር ጥያቄ በአዲስ መልክ የብድር ውል መያዝ አለበት፣

4. ተጨማሪ ብድር የሚፈቀደው ከቀድሞው ብድር ላይ 75 በመቶና በላይ የሚሆነው ብድር መከፈሉ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡
5. ተጨማሪ ብድር ጥያቄ ሊፈቀድ የሚችለው ከዚህ በፊት የተሰጠው ብድር ውጤታማ ወይም ትርፋማ በሚያደርግ ተግበር መዋሉ ከተረጋገጠና በተጨማሪነት የተጠየቀው ብድር ውጤታማ ይሆናል ተብሎ ሲታመን ብቻ ይሆናል፣
6. ለተጨማሪ ብድር የሚፈቀደው የብድር መጠን ከዚህ በፊት ከነበረው ብድር ውስጥ በቀሪ ዕዳነት ከተመዘገበው መጠን መብለጥ የለበትም፣

29. <u>ስለ ብድር ክትትልና ቁጥጥር</u>

1. የኅብረት ስራ ማህበራት በብድር አሰጣጥና አሰባሰብ ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋሉ፣

2. ኅብረት ስራ ማህበራት በወቅቱ ያልተመለሰ ብድር ከተበዳሪዎች መሰብሰብ እንዲቻል ክፍያ ያዘገየውን ተበዳሪ ሥም፣ ያቀረባቸውን ዋሶች ወይም ያስያዘውን ዋስትናና ያልተሰበሰበውን የብድር መጠን፣ ብድሩ ገቢ ሣይሆን የቆየበት ጊዜ እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን በማጥናትና ተበዳሪውን በማነጋገር ገንዘቡን በወቅቱ ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ የብድር ኮሚቴው ወይም ብድር ባለሙያው የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርበታል፡፡

ሀ/ የብድር ኮሚቴው ወይም የብድር ባለሙያዉ የብድር ክፍያ በተቋረጠ በመጀመሪያዎቹ እስከ 10 ቀናት የተቋረጠበትን ምክንያት ማጣራትና ተበዳሪዎችንና ዋሶችን በማነጋገር ክፍያው ወዲያውኑ

የሚቀጥልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

ለ/ በተደረገው ውይይት ክፍያውን እስከ 15 ቀናት ድረስ መክፈል ካልጀመረ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለተበዳሪውና ለዋስ/ሶች ይሰጣል፣

ሐ በተሰጠው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መሠረት ተገቢውን ክፍያ ካልፈፀመ ሥርዓቱን ተከትሎ እርምጃ ይወሰዳል፣

3. ለብድር አገልግሎት የሚውለው ገንዘብ ከጠቅላላው ሀብት ከ70-80 በመቶ መብለጥ የለበትም፣
4. የኅብረት ስራ ማህበሩ የሚበደረው ብድር የመመለስ አቅሙን ያገናዘበ ይሆናል፣
5. የኅብረት ስራ ማህበሩ ከሰጠው ጠቅላላ ብድር ውስጥ ጠቅላላ የማይመለስ ብድር ከ3 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

30. በወቅቱ ላልተመለሰ ብድር ስለሚወሰድ ህጋዊ እርምጃ

1. ከተበዳሪዎች ጋር ድርድር ይካሄዳል፡፡ በድርድሩ መሰረት ተበዳሪው ብድሩን ለመመለስ ፈቃደኛ ከሆነ ብድሩን ለማስመለስ የወጡ ወጭዎች፣ ወለድና ዋናው ለኅብረት ስራ ማህበሩ እንዲከፍል ይደረጋል፣
2. በድርድሩ መሰረት ተገቢውን ክፍያ ካልፈፀመ ሥርዓቱን ተከትሎ የዕዳ ማካካስ ሥራ ይሰራል፣
3. የዕዳ ማካካስ ስራ ተሰርቶ ዕዳው ካልተሸፈነ በቀሪው ዕዳ በመደበኛ ፍርድ ቤት ተከሶ ብድሩን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 29.2 እና 29.3 በተጠቀሰው የብድር አመላለስ ሥርዓት ብድር የመለሰ ተበዳሪ በህብረት ስራ ማህበሩ ጥቁር መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል፡፡
5. በኅብረት ስራ ማህበሩ ጥቁር መዝገብ የተመዘገበ ተበዳሪ አባል በቀጣይ

የብድር አገልግሎት የሚያገኘው ጠቅላላ ጉባኤ ሲፈቅድ ብቻ ይሆናል፡፡

31. የማይመለስ ብድር ስለማካካስ

1. ለማይመለስ ብድር ማካካሻ የሚሆን መጠበበቂያ በኅብረት ስራ ማህበራት የሂሳብ ዓመት ተወስኖ መቀመጥ አለበት፣
2. የማይመለስ ብድር ከማይመለስ ብድር መጠባበቂያ ሂሳብ መሸፈን አለበት፣ የማይመለስ ብድር መጠባበቂያ የሚካካስበት ሁኔታም በሚከተለው አግባብ ተፈፃሚ ይሆናል፡-

ብድሩ ሳይመልስ የዘገየበት ጊዜ በቀን	የሚካካስ የብድር መጠን በመቶኛ
ከ1-30	0
ከ31-90	35
91-180	50
181-365	75
ከ365 ቀን በላይ	100

3. ያልተመለሰ ብድርም ሆነ የማይመለስ ብድር በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ እንዲሰረዝ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የኅብረት ስራ ማህበራት አመራሮች ብድሩ እንዲመለስ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው፣
4. የማይመለስ ብድር የሚሰረዘው የኅብረት ስራ ማህበራት ኦዲት ከተደረገና የተቋሙ የሂሳብ አቋም በኦዲተር ከተረጋገጠ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባዔ ከፀደቀ በኋላ ነው፣
5. የኅብረት ስራ ማህበራት የማይመለስ ብድርን ከብድር መዝገብና ሃብትና ዕዳ መግለጫ ሰርዞ በመመለሻ ጊዜው ባልተመለሰ ብድር መከታተያ መዝገብ ላይ በመመዝገብ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ አለበት፣
6. በመመለሻ ጊዜው ያልተመለሰ ብድር ከተሰረዘና ከተካካሰ በኋላ ዋናና ወለዱ በተለያዩ ስልቶች ሲመለስ ዋናው በኅብረት ስራ ማህበሩ ካፒታል ሥር

ሆኖ የብድር ኪሳራ ታሣቢ መጠባበቂያ ተብሎ ሲመዘገብ ወለዱ በኅብረት ስራ ማህበሩ ልዩ ልዩ ገቢ ይመዘገባል፡፡

7. ከተሰረዘ ብድር የሚመለስ ገንዘብ በማህበሩ ህጋዊ ደረሰኝ ገቢ መሆን ይኖርበታል፡፡

ክፍል ስድስት

የሰነድ አያያዝና የፋይናንስ ግብይት ትስስር

32. የብድር ሰነድ አያያዝ

1. የብድር ሰነድ በጥንቃቄ መያዝ ይኖርበታል፣
2. ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ የሰነድ አይነቶች፣

ሀ/ የተበዳሪው ማመልከቻ፣

ለ/ የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ የውሳኔ ሃሳብ፣

ሐ/ ደጋፊ ማስረጃዎች፣

መ/ የብድር ቅፆች፣

ሠ/ የብድር ውል፣

ረ/ በብድር አፅዳቂ አካል የተፈረመባቸው ሰነዶች፣

ሰ/ የወጪ ማዘዣዎች፣

ሸ/ ተከፍሎ ያለቀና ገና በመክፈል ላይ ያለ ብድርን የሚያመለክቱ ሰነዶች፣

ቀ/ በዋስትናነት የተያዙ ንብረቶች፣ የንብረቶቹ ህጋዊ ማረጋገጫ ሰነዶች ወይም ህጋዊ ማስረጃዎች

በ/ ሌሎች ተፈላጊ ሰነዶች

3. የብድር አገልግሎት የተፈፀመባቸው ሰነዶች ለተተኪ ኮሚቴ አባላት ወይም ለብድር ባለሙያ በጥንቃቄና በዝርዝር ማስረከብ ይገባል፣

4. ከጥንቃቄ ጉድለት የጠፉ ሰነዶች ቢያጋጥሙ በኃላፊነት ያስጠይቃል፡፡

33. የፋይናንስ ግብይት ትስስር

1. የፋይናንስ ግብይት ትስስር የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥም የአባላትን የብድር ፍላጎት ለማሟላት እንዲቻል የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የማበደር ፍላጎትና አቅም ካላቸው ተቋማት ጋር የጋራ ጥቅም በሚያስገኝ መልኩና ውጤታማነት ባለው ሁኔታ የሚደረግ ትስስር ነው፡፡
2. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በፋይናንስ ግብይት ትስስር መበደር የሚችሉባቸው ተቋማት፤
   - ሀ/ በኅብረት ስራ አዋጅ ከተቋቋሙ የኅብረት ስራ ማህበራት፣
   - ለ/ ከባንኮች፣
   - ሐ/ ከአነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋማት፡፡
3. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በፋይናንስ ግብይት ትስስር

ማበደር የሚችሉት በኅብረት ስራ አዋጅ 985/2009 አንቀፅ 48 መሰረት ይሆናል፡፡

4. የብድር ትስስር መርሆዎች፤

ሀ/ የብድር ትስስር መፈፀም ያለበት ከተቋም ጋር እንጂ ከግለሰብ ጋር መሆን የለበትም፣

ለ/ ትስስር መፍጠር ያለባቸው ጠንካራ የቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር መሆን ይኖርባቸዋል፣

ሐ/ ትስስሩ የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፣

34. <u>በብድር ትስስር መታየት ያለበት ቅድመ ሁኔታ</u>

1. የቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማህበራት የብድር ትስስር ከማድረጋቸው በፊት ከአባላት እና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ

አግባብ ካለው ባለስልጣን ጋር ውይይት ማድረግ አለባቸው፣

2. የበጀት ዓመቱ ብድር በዕቅድ ተይዞ በጠቅላላ ጉባዔ በ2/3ኛው አባላት መፅደቅ አለበት፣
3. የብድር ትስስሩን ለመተግበር የወሰነ የኅብረት ሥራ ማህበር ትስስሩን መምራት የሚችል አስተዳደራዊ መዋቅር ሊኖረው ይገባል፣
4. ሁለቱም የግብይት ትስስር የሚፈጥሩ ተቋማት አብሮ ለመስራት የሚያስችላቸውን ግልጽ ዓላማ፣ ግብ፣ የሁለቱም መብትና ግዴታ እና ሊያሰራቸው የሚችል የሕግ ማዕቀፍ መኖሩን ማረጋገጥ፣
5. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አስተዳደርና የሂሳብ አያያዝ

ዘመናዊ አሰራርን የተከተለ መሆን ይኖርባቸዋል፣

6. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን የሂሳብ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ሪፖርት እና የብድር አመላለስ ታሪክ መረጃ ማደራጀት ይኖርባቸዋል፣

36. <u>**የብድር ትስስር ሲደረግ መሟላት ያለባቸው**</u>

1. ማንኛውም የብድር ትስስር ተፈፃሚ የሚሆነው በአበዳሪና በተበዳሪ መካከል በህግ ፊት ተቀባይነት ያለው ውል ሲኖር ብቻ ነው፤
2. አበዳሪና ተበዳሪ ለሚፈፅሙት ብድር በውል ላይ የተመሰረተ አሰራሮችን መከተል ይኖርባቸዋል፣

3. ሁለቱም አካላት ጥቅሙ የጋራ መሆኑን በመረዳት ተደጋግፈው መስራት አለባቸው፤

4. የብድር ትስስር ለመፍጠር የሚከተሉትን ዋና ዋና መረጃዎች መሟላት አለባቸው

ሀ/ አግባብ ባለው ባለስልጣን የተረጋገጠ የ3 ዓመት ተከታታይ የኦዲት ሪፖርት፣

ለ/ የተቋሙን ውጤታማነት የሚያሳይ መረጃ

ሐ/ የተቋሙን የብድር አመላለስ ታሪክ የሚያሳይ መረጃ

መ/ የንግድ ስራ እቅድ ፡፡

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

37. <u>ስለ ተጠያቂነት</u>

ማንኛዉም የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሶ የተገኘ ሰው አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

38. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

39. <u>መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኅብረት ስራ ኤጀንሲ ከጸደቀበት ከሚያዚያ ወር 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ግዛቸው ዓሊ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ

ዋና ዳይሬክተር

አባሪዎች

አባሪ 1

ለ----------------- የቁጠባና ብድር ኃ.የተወሰነ የኅብረት ስራ ማህበር

የብድር ጥያቄ ማመልከቻ

ቀን_______

የአባልነት መ/ቁጥር________

ሙሉ ስም_____________ ዕድሜ ________ ፆታ_

አድራሻ ከተማ_______ ’ክፍለ ከተማ_________

’ወረዳ_________

የቤት ቁጥር________፣ ስልክ ቁጥር _______ ፣ኢሜል-------------------------

የጋብቻ ሁኔታ ያገባ -----የትዳር አጋር ስም------------------------------- ያላገባ-------

የስራ ሁኔታ የመንግስት-------- መ/ያልሆነ ---------- የግል------------

የተበዳሪ ወርሃዊ ገቢ መጠን ------------- የትዳር አጋር ወርሃዊ የገቢ መጠን-------------- ጠቅላላ ወርሃዊ ገቢ-------------

የተጠየቀው የብድር መጠን በአሃዝ_____

በፊደል_____________________

የብድር ዘመን____________________

ብድሩ የተፈለገበት ምክንያት _________________________

የዋስትና አቀራረብ የተበዳሪው ቁጠባና ዕጣ በብር-----------

ከተበዳሪው ቁጠባና ዕጣ በተጨማሪ ለብድር ማስያዣነት የቀረበ የዋስትና አይነት

ዋስ የሚሆኑ አባላት ቁጠባና ዕጣ በብር-----------

ወርሃዊ ደመወዝ በብር--------------------

ቋሚ ንብረት ግምት በብር -------------

ቦንድ በብር --------------

ከዚህ በፊት የተወሰደ ብድር በብር _______________

ከሌላ አበዳሪ ተቋም የተወሰደ ብድር ካለ በብር-------------

- ብድሩን የሰጠው ተቋም------------

ከማመልከቻው ጋር በአባሪነት የተያያዘ ማመልከቻ፡-

ዝርዝር	ብዛት
_____________________	_______
_____________________	_______

ከላይ የተጠቀሰው የብድር መጠን እና ያቀረብኩት የብድር ዋስትና ዋስትና ማስረጃ ትክክል መሆኑን እያረጋገጥኩ የሚሰጠኝን ብድር ባቀርብኩት ማስረጃ መሰረት ብድሩ እንዲፈቀድልኝ እጠይቃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ስም________

ፊርማ________

አባሪ 2

<u>የብድር ጥያቄ መገምገሚያ</u>

የ---------------- የቁጠባና ብድር ኃ.የተወሰነ

የኅብረት ስራ ማህበር

1. አጠቃላይ የተበዳሪው ሁኔታ
   - ሙሉ ስም________________ዕድሜ ----------
     ፆታ --------
   - አድራሻ ከተማ_______ ፣
     ክፍለከተማ_______፣ወረዳ__________
   - የቤት ቁጥር_______፣ ስልክ ቁጥር _______
     ፣ኢሜል-------------------------
   - የጋብቻ ሁኔታ ያገባ -----የትዳር አጋር
     ስም------------------------------- ያላገባ-------
   - የስራ ሁኔታ የመንግስት--------
     መ/ያልሆነ ---------- የግል------------

- የተበዳሪው ወርሃዊ ገቢ መጠን -------------
  የትዳር አጋር ወርሃዊ የገቢ መጠን-------------
  - ጠቅላላ ወርሃዊ ገቢ-------------
- የትምህርት ደረጃ ____________
- በህብረት ስራ ማህበሩ አባል የሆነበት ጊዜ
  ____
- ከኅብረት ስራ ማህበሩ ጋር በተያያዘ በወንጀል ተከሶ ያልተፈረደበት_________

2.የተበደሪው አቅም ሁኔታ

- ቋሚ ንብረት __________ ፣ተንቀሳቃሽ __________፣__________የተጣራ ካፒታል ____________________ ፣ ዕዳ ____________________
- ለመስራት ላሰበው ስራ ተበዳሪው የመደበው ሀብት መጠን በብር ___________________
- ለመስራት የፈለገውን ስራ ለማከናወን የተበዳሪው ሀብት ተመጣጣኝነት_________ ______________________________________ ___________
- የስራው ሁኔታ አዲስ ______________________ ፣ የተለመደ ________________

3. ተበዳሪው ዕቅዱን ለመፈፀም ያለው ብቃት፣

- ተበዳሪው እሰራ ያለው ስራ ከዕቅዱ ጋር ያለው አግባብነት/ ተዛማጅነት

____
____
____
____
____

- ○ ስራው ተበዳሪው ከሚሰራው ስራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ከሌለው እንዴት ለመፈፀም አስቧል

____

____

- ○ በስራው ላይ ለማሰማራት የተፈለገው የሰው ሀይል ________________
- ○ ያላቸው ችሎታ____________________________
- ○ በአካባበው የሰው ሀይል በበቂ ሁኔታ መገኘት________________
- ○ ተበዳሪው ድጋፍ የሚያገኝ ከሆነ ከነማን? እንዴት?

____
____
____

4. የተበዳሪው የዋስትና ሁኔታ፣

- በኅብረት ስራ ማህበሩ ያለው የገንዘብ መጠን

____

- ተጨማሪ ያቀረበው ዋስትና

____
____
____
____

- ለቀረበው ዋትና ህጋዊ ማረጋገጫ

  ____
  ____
  ____

- ዋስትናው አሁን በገበያ ያለው ግምታዊ ዋጋ

  ____

- ዋስትናው ቶሎ ወደ ገንዘብ የመለወጥ ሁኔታ

  ____

- ዋስትናው ያለበት ደረጃ

  ____

- የዋስትናው አጠባበቅ ሁኔታ

  ____

- ግለሰብ ዋስ ከሆነ የቀረበው ማስረጃና ተቀባይነት

  ____
  ____
  ____

- የቀረበው ዋስትና ለብድሩ መጠን ያለው ተመጣጣኝነት ___________________________

5. የስራ አካባቢ ሁኔታ

- በአካባቢው ያለው ሰላም ሁኔታ

  ____

- አካባቢው ለስራ ምቹነት_____________________________________

  ____

- ለሚመረተው ምርት ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት ለገበያ ያለው ቅርበት
____
____

- ለክትትልና ቁጥጥር ያለው አመችነት________________________

- ስራው ለአካባቢው ብህልና እምነት ያለው ተያያዥነትና ተቀባይነት
____
____
____
____

- የምርቱ ወይም የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ፍላጎት______________________________
____
____

- የአካባቢውን ተፈጥሮ ምርቱ ወይም አገልገሎቱ የማይፃረር መሆኑ____________________
____
____

6. የተበዳሪው ብድር አመላለስ ሁኔት

- ባለፉት አመታት ውስጥ የተበዳሪው የብድር አወሳሰድና አመላለስ ሁኔታ

	የተሰጠ	ቀን	ተመለሰ	ቀን
1.	________________	________	______	_____
2.	________________	________	______	_____
3.	________________	________	______	_____

- ሳይመለስ በዕዳነት ተመዝግቦ ያለ ብድር

  ____

- ብደሩ ሳይመለስ የቆየበት ጊዜ

  ____

- ብድር አመላለሱ በብድር ውሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት ስለመሆኑ__________

- ብድሩ ያልተመለሰበት ምክንያት

  ____
  ____
  ____

- የብድር ጊዜ እንዲራዘም የተጠየቀ ከሆነ

  ____

- ብድሩ ማራዘም ያስፈለገበት ነምክንያት

  ____
  ____
  ____

- ተጨማሪ ብድር የተሰጠ ከሆነ መጠን

  ____

- ተጨማሪ ብድር የተሰጠበት ምክንያት
____
____

- ተበዳሪው አባል ከሆነ ኀብረት ስራ ማህበሩ የሚሰጠውን ኃላፊነት የመወጣት ሁኔታ
____

- ተበዳሪው ከሌላ የብድር ተቋም የወሰደው ብድር መጠን _____________

አመላለስ___________

- በብድር አመላለስ ወቅት በማህበሩ ወይም በሌላ ተቋም የቀረበበት ክስ ካለ፣
- በኀብረት ስራ ማህበሩ የቀረበበት ክስ መጠን________ ፣ በሌላ ተቋም ________
- ክሱ ያለበት ሁኔታ_________________’ የተሰጠ ውሳኔ__________
- ከዚህ በፊት የተሰጡትን ብድሮች ለተባለለት አላማ ማዋል_________________________________

7. የተጠየቀው ብድር ሁኔታ

- የተጠየቀው ብድር መጠን በብር ________________ / _________________/

- ብድሩ የሚፈለግበት ምክንያት
____

- የብድር ዘመን___________________________
- የብድር አመላለስ ሁኔታ በ________ ቀናት ለ ________ ጊዜ '

8. የውሳኔ ሃሳብ ፣

____
____
____
____
____

ከላይ ከ1-7 ባሉት መገምገሚያ ነጥቦች መነሻ መሰረት የተበዳሪውን ሁኔታ በመገምገም የተጠቀሰውን የውሳኔ ሃሳብ ተሰጥቷል።

ስም	የስራ ድርሻ	ፊርማ	ቀን
1 --------------------------------	----------------	-----------	-----------------------
2. --------------------------------	----------------	-----------	-----------------------
3. --------------------------------	----------------	-----------	-----------------------

የስራ አመራር ኮሚቴ ውሳኔ፣

____
____
____
____
____
____

ስም   የስራ ድርሻ
ፊርማ   ቀን

1 -------------------------------   ----------------
-----------   -----------------------

አባሪ 3

የብድር ውል

ውል ሰጭ

ከዚህ በታች ውል ሰጭ ተብሎ የመጠቀሰው የ_________ ______ ኃላፊነቱ የተወሰነ የቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር

ውል ተቀባይ

ከዚህ በታች ውል ተቀባይ ተብሎ የሚጠራው_______ _________ መካከል የተደረገ የብድር ውል

1. አጠቃላይ

1.1 ውል ተቀባይ በዚህ ውልና ሌሎች ኅብረት ስራ ማህበሩ በሚተዳደሩባቸው ህጎች መሰረት ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን በብድር አግኝቷል፣

1.2 ብድሩ ለ_____________ ዓላማ የሚውል ይሆናል፣

1.3 ብድሩ ________ጊዜ ብድር ሲሆን ለ_______ ቀናት/ወራት/ አመታት ይቆያል፣

1.4 የብድር መጠን ብር _______ /________________ / ይሆናል፣

2. የብድር ገንዘብ አፈቃቀድ

2.1 ብትሩ በ __________ቀናት/ ወራት/ አመት ክፍያ ውል ተቀባይ ለመውሰድ ተስማምቷል፣

2.2 ከመጀመሪያ ክፍያ በኂላ የሚደረግ የብድር ክፍያ ውል ተቀባይ ከዚህ በፊት የተፈቀደለትን ብድር አጠቃቀም ተገምግሞ የሚፈቀድለት መሆኑን ተስማምቷል፣

2.3 ውል ተቀባይ የወሰደውን ብድር ባቀረበው የስራፅቅድ መሰረት ካልፈፀመ ውል ሰጭ የሰጠውን ብድር ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ ያስመልሳል

3. የወለድ ሁኔታ

3.1. ውል ተቀባይ _____ በመቶ የሚሆን ወለድ በዓመት በውሉ ላይ በተቀመጠው የክፍያ ጊዜ

ከዋና ብድር ገንዘብ ጋር ለመክፍል ተስማምቷል፣

3.2. ውል ተቀባይ የብድር ክፍያ ጊዜ ካሳለፈ ከሚከፈለው የወለድ መጠን በተጨማሪ ____________ በመቶ ወለድ ክፍያ ላለፈበት ብድር መጠን ይከፍላል፣

3.3. የወለድ ተመን ለውጥ ውል ሰጭ በሚያደርግበት ወቅት በፅሑፍ ወይም አመቺ በሆነ መንገድ ለውል ተቀባይ ያሳውቃል፣

4. የዋስትና ሁኔታዎች

4.1. ውል ተቀባይ ላቀረበው የብድር መጠን በውል ሰጭ በተለያዩ ሁኔታ ያስቀመጠው ቁጠባና ዕጣ መጠን ለዋስትናነት አቅርቧል፣

4.2. ውል ተቀባይበተራ ቁጥር 4.1 በላይ ለሚሆነው ብድር መጠን ለዋስትናነት፡-

4.2.1. ______________________________________ ________________

4.2.2. ______________________________________ ________________

4.2.3. ____

4.2.4. ____

ያቀረበ ሲሆን ዋስትናዎቹም በህግ እውቅና ያላቸው መሆኑን ውል ሰጭ አረጋግጧል፣

4.3. በኅብረት ስራ ማህበሩ ውስጥ እያደገ የሚሄደው የውል ተቀባይ የገንዘብ መጠን በውል ሰጭ በዋስትናነት እንዲያገለግል ተስማምቷል፣

4.4. በዋስትናት የቀረቡ ግለሰቦች ለውል ተቀባይ ዋስ መሆናቸውን በውል ሰጭ ፊት በግንባር ቀርበው በፊርማ አረጋግጠዋል፣

5. የብድር አመላለስ

5.1. ውል ተቀባይ በየ__________ ቀናት ውስጥ ለውል ሰጭ፣

5.1.1. ዋና ብር _______/____________________/

5.1.2. ወለድ ብር______/____________________/

5.1.3. ድምር ብር______/____________________/

በተከታታይ በ_________ ጊዜ ገደብ ውስጥ ለመክፈል ተስማምቷል፣

5.2. ውል ሰጭ ውል ተቀበይ ገንዘቡን ለመመለስ እንዲችል በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

5.3. ውል ሰጭ ውል ተቀባይ ብድሩን በሚከፍልበት ጊዜ አስፈላጊውን ህጋዊ ማስረጃዎች ይሰጠዋል፣

5.4. ውል ሰጭ ውል ተቀባይ ብድሩን በሚመልስበት ወቅት በአንድ ጊዜ ወይም በመከፋፈል ብድሩን ማሰባሰብ ይችላል፣

5.5. ውል ተቀባይ በብድር ውሉ ላይ ከተቀመጠው በፊት ብድሩን ለመክፈል ቢፈልግ ውል ሰጭ ለመቀበል ተስማምቷል፣

6. ግዴታዎችና ኃላፊነቶች

6.1. ውል ተቀባይ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ቢያፈርስ ወይም ለኅብረት ስራ ማህበሩ ህጎች ተገዢ ካልሆነ ውል ሰጭ ብድሩን እንዲመልስ ያስገድደዋል፣

6.2. ውል ተቀባይ ብድሩን በሚፈለግበት መክፈያ ጊዜ ካሳለፈ በተራ ቁጥር 3.2 የተቀመጠው

እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ ____________ በመቶ ቅጣት ያስከፍላል፣

6.3. ውል ተቀባይ ግዴታውን ካልተወጣ በዋስትና ያስያዘውን ውል ሰጭ ሊያስከብር ይገደዳል፣

6.4. ው ሰጭ ውል ተቀባይ ግዴታዎችን በአግባቡ እንዲወጣአስፈላጊውን እገዛና ምክር ይሰጣል፣

6.5. ውል ሰጭ ብድሩን በተቀመጠው ጊዜ እንዲመለስ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣

ይህ የብድር ውል ዛሬ ______________________ ቀን ________________ ዓ.ም በውል ሰጭና በውል ተቀባይ መካከል ተፈረመ::

<u>ውል ሰጭ</u> <u>□ል ተቀባ□</u>

ስም______________________

ስም______________

ፊርማ_______________

ፊርማ______________

ቀን_____________________

ቀን______________

<u>ዋሶች</u>

<u>ስም</u> <u>ፊርማ</u>

<u>ቀን</u>

1	__________	__________
2	__________	__________
3	__________	__________

<u>እማኞች</u>

	ስም	ፊርማ
1	________________	__________
2	________________	__________
3	________________	__________

አባሪ 4 የብድር መከታተያ መዝገብ

ተ.ቁ	የተበዳሪው ስም	መለያ ቁጥር	የአባሉ የእጣ መጠን /በብር/	ጠቅላላ የአባሉ መደበኛ ቁጠባ መጠን /በብር/	የተበደረው ገንዘብ መጠን	የተበደረበት ቀን	የብድር ቆይታ ጊዜ	በየጊዜው የሚመለሰው የብድር መጠን	ብድሩን ከፍሎ የሚያጠናቅቅበት ቀን	የተበደሩበት ምክንያት

አባሪ 5 የብድር መከታተያ ቅፅ፣

የተበዳሪው ሙሉ ስም--
መለያ ቁጥር ....
አድራሻ -------------------------------

የተፈቀደ ገንዘብ መጠን			የተሰጠ ብድር መጠን			መመለስ ያለበት ብድር		የተመለሰ ብድር			ቀሪ		ውዝፍ	
ቀን	ብር	ሳ	ቀን	ብር	ሳ	በዚህ	በዚህ	ቀን	ብር	ሳ	ከዋና /ብር	ከወለድ /ብር	ከዋና /ብር	ከወለድ /ብር

ቅፁን ያዘጋጀው ስም... ያፀደቀው ....
ፊርማ .... ፊርማ................................

አባሪ 6 የብድር አፈፃፀም ሪፖርት ቅፅ፣

ተ.ቁ	የተበዳሪ አባላት ዝርዝር	የተፈቀደ ገንዘብ መጠን		የተሰራጨ ብድር		መመለስ ያለበት ብድር		የተመለሰ ብድር			ቀሪ እዳ	
		ብር		ብር		በዚህ …………	እስከዚህ ………….	ቀን	ብር	ሳ	ከዋና /ብር	ከወለድ /ብር
ድምር												

የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ ስም ---------------------------------

ፊርማ------------------------

ቀን ---------------------------